ልጄ ሆይ አሏህን ብቻ ተገዛ

በወጣቱ ተልዕኮ

አህመድ የሱፍ



O my child worship Allah alone

ልጄ ሆይ አሏህን ብቻ ተገዛ

በወጣቱ ተልዕኮ

አህመድ የሱፍ

All right reserved

© የወጣቱ ተልዕኮ
የወጣቱ ተልዕኮ የኦንላይን እትም 2010
ሰሜን ወሎ ወልድያ

ahmedyesuf29@gmail.com

+251927790323

https://youth-mission.com



የወጣቱ ተልዕኮ

Presented by: Youth-Mission
Online Amharic Islamic Books
Publishing.


بسم الله الرحمن الرحيم

በአሏህ ማመን ማለት



- አሏህ የሁሉም ነገር ጌታ እና ባለቤት ነው
- ብቸኛ ፈጣሪ እሱ ብቻ ነው።
- የዚህ ፍጥረተ አለም ጉዳዮች አስተናባሪ እሱ ነው።
- አምልኮ ያለ አጋር ያለ ባላንጣ የሚገባው እሱ አሏህ ብቻ ነው። ከእሱ ውጭ ያሉ ጣኦታት አማልክት ውሸት ናቸው። እነሱን ማምለክ ጥመት ነው። ትርፉ ኪሳራ ብቻ ነው።

አሏህ እንዲህ አለ፡ “እውነቱ እሱ አሏህ ነው። ከእሱ ውጭ የሚለምኑት ነገር እሱ ባጢል (ውሸት) ነው። በእርግጥ! አሏህ የሁሉ የበላይ ታላቅ ነው።” {አል-ቁርአን 22፡62}

መልመጃ ፣

ቀለምመቀባት



በአሷህ ማመን

አሷህ የሁሉም ጌታ ነው

ብቸኛው ፈጣሪ አሷህ ነው

ሊመለክ የሚገባው አሷህ ብቻ ነው።

የተውሂድ ክፍሎች



ሶስት የተውሂድ አይነቶች አሉ።

- ተውሂደ ሩቡቢያ
- ተውሂደል ኡሉሂያ
- ተውሂደል አስማኡ ወሲፋት

በአሏህ ማመን ሶስቱን የተውሂድ ክፍሎች አጠቃሎ ይይዛል።


መልመጃ 2

ሶስቱን የተውሂድ ክፍሎች ....ውስጥ ፃፍ

ተውሂደ ሩቡቢያ

ተውሂደል ኡሉሂያ

ተውሂደል አስማኡ ወሲፋት



ተውሂደ ሩቡቢያ



የዚህ ፍጥረተ አለም ፈጣሪ አሏህ ብቻ እንደሆነ ማረጋገጥ እና መመን ነው።

የጉዳዮች ሁሉ አስተናባሪ አሱ ነው።

ህይወት የሚሰጠው እና የሚነጥቀው ሞትን የሚያስከትለው እሱ ነው። ሁሉን ሰጭ ፣ ሁሉን ነሽ ሃያል ፣ ጥበበኛ ነው።

ይህ የተውሂድ ክፍል ማረጋገጥ እና ማመን በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ያለ የተተከለ ነው።

መልመጃ 3

ባዶ ቦታውን በተስማሚ ቃላት ሙሉ

ህይወትን እና ሞትን ሰጭ አንድ የአሏህ ብቻ ነው። ሁሉን ሰጭ ሁሉን ነሽ ነው። የዚህ ፍጥረተ አለም ፈጣሪ እሱ ነው።

- ተውሂደ ሩቡቢያ ማለት _____ አሏህ ብቻ እንደሆነ ማረጋገጥ እና ማመን ነው።
- የጉዳዮች ሁሉ_____እሱ ነው
- እሱ_____ሃያል ፣ ጥበበኛ ነው።

ተውሂደል ኡሉሂያ



ሁሉንም የአምልኮ ተግባራቶች ለአሏህ ብቻ ማድረግ ነው። አሏህን በአምልኮት መነጠል ነው።

ኡሉሂያ ማለት ኢባዳ ነው።

አሏህ ማለት ብቻውን የሚመለክ ነው።

ኢባዳ ማለት ደግሞ

ኢባዳ ማለት አሏህ የሚወደው ማንኛውም አይነት ተግባር ነው። አሏህ የሚወደው ማንኛውም በንግግር እና በተግባር የሚገለጽ በድብቅም ሆነ በግልፅ የሚሰሩ ተግባራቶችን የሚገልፅ ነው።

መልመጃ 4

የሚከተሉትን አዛምዱ



ተውሂደል ኡሉሂያ	አሏህ የሚወደው ማንኛውም በንግግር እና በተግባር የሚገለጽ ፣ በድብቅም ሆነ በግልፅ የሚሰሩ ተግባራቶች ናቸው፡፡
ተውሂደል ኡሉሂያ	ብቻውን የሚመለክ
ኢባዳ	በሁሉም የአምልኮ ተግባራት አሏህን መነጠል ነው፡፡

ተውሂደል አስማኡ ወሲፋት



አሏህ ለእራሱ ያረጋገጠውን ወይም መልእክተኛው ለእሱ ያረጋገጡትን ፍፁም እንከን የለሽ የሆኑ ስምና ባህርያቶችን ማረጋገጥ ነው።

አሏህ ለእሱ ውድቅ ያደረገውን ወይም መልእክተኛው ለእሱ ውድቅ ያደረገትን እንከን አልባ ያልሆኑ ስምና ባህርያቶች ውድቅ ማድረግ ነው።

ሃያሉ አሏህ እንዲህ አለ

‹‹እሱን የሚመስል ምንም ነገር የለም። እሱ ሁሉን ሰሚ ፣ ሁሉን አዋቂ ነው።››
(አሹራ 11)

መልመጃ 5

ባዶ ቦታዎቹን በተስማሚ ቃላቶች አሟሉ::

ተውሂደል አስማኡ ወሲፋት

————ለእሱ ያረጋገጠውን ወይም——— ——ለእሱ ያረጋገጡትን ስምና ባህሪያቶች ማረጋገጥ ነው::

መልአክቶች ፣ አሏህ ፣ የሰው ልጆች ፣ መልእክተኛው

————ለእሱ ውድቅ ያደረገውን ወይም————ለእሱ ውድቅ ያደረገትን እንከን አልባ ያልሆኑ ስምና ባህርያቶች ውድቅ ማድረግ ነው::



ሁለተኛው መርህ

በመልአክቶች ማመን ከእምነት መሰረቶች ውስጥ አንዱ ነው።

በሐዲሱ ጅብሪል እንደተገለፀው የአሏህ መልእክተኛ አለ

ኢማን ማለት በአሏህ ማመን ፣ በመጽሐፍቶቹ ፣ በመልእክተኞቹ ፣ በመጨረሻው ቀን እና ጥሩም ሆነ መጥፎ የሆነው እና የሚሆነው ነገር ሁሉ በአሏህ ውሳኔ ነው ብሎ ማመን ነው።

ሙስሊም

መልመጃ 6

ሐዲሱ በተዘገበበት አግባብ እነዚህን ቁጥሮች (1፣2፣3፣4፣5፣6) በመጠቀም ቃላቶቹን አስተካክላችሁ ፃፉ።።

በሐዲሱ ጅብሪል እንደተዘገበው የአሏህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ።።

ኢማን ማለት

( ) ጥሩም ይሁን መጥፎ የሚሆው ነገር ሁሉ በአሏህ ውሳኔ ነው ብሎ ማመን

( ) በአሏህ ማመን

( ) በመልአክቶች ማመን

( ) በመጨረሻው ቀን መመን

( ) በመጽሐፍቶቹ ማመን

( ) በመልአክቶቹ ማመን

በመልአክቶቹ ማመን



ሁለተኛው መርህ

በመልአክቶቹ ማመን የሚተለትን ነገሮች ይይዛል፡፡

- መኖራቸውን ማመን
- የተከበሩ የአሏህ ባሮች
- አገልጋዮች መሆናቸውን
- ለአምልኮቱ እና ለትእዛዙ አሏህ የፈጠራቸው መሆኑን

መልመጃ 7

ለትክክለኛው አረፍተ ነገር ይህን ☑ ምልክት አስቀምጡ። ስህተት ለሆነው አረፍተ ነገር ደግሞ ይህን ☒ ምልክት አስቀምጡ።

በመልአክቶች ማመን የሚከተሉትን ነገሮች ይይዛል።

- ✍ መኖራቸውን አለማመን
- ✍ የተከበሩ የአሏህ ባሮች መሆናቸውን
- ✍ አሏህ የፈጠረቸው ለእሱ አምልኮ እና ትእዛዝ ነው።

በመለኮታዊ መጽሐፍቶች ማመን



ሶስተኛው መርህ

በመለኮታዊ መጽሐፍቶች ማመን ከኢማን ምሰሶዎች ውስጥ አንዱ ነው። በእነሱ ማመን ማለት እውነተኛ እና ትክክለኛ የሃያሉ አሏለህ ንግግሮች መሆናቸውን ከልብ ማመን ነው።

በውስጣቸው መመሪያ የያዙ ለወረደላቸው ህዝቦች በቂ ያቸው የሆነ ነው።

አሏህ ስማቸውን በጠቀሳቸው እና ባልጠቀሳቸው መጽሐፍት እናምናለን።

መልመጃ 8



በመለኮታዊ መጽሐፍቶች ማመን አለማን ምሰሶዎች ውስጥ አንዱነው።

ቀለም መቀባት

በመልዕክተኞች ማመን



አራተኛው መርህ

በመልዕክተኞች ማመን ከኢማን መሰረቶች አንዱ ነው። ምክኒያቱም በአሏህ እና በፍጥረቱ መካከል ያለ መልዕክትን የሚያደርሱ እና በፉጡሮቹ ላይ ማስረጃ የሚሆኑ ናቸው።

በእነሱ ማመን ማለት በመልእክታቸው እና በነብይነታቸው ማመን ነው። ስለ አሏህ ባስተማሩት ነገር ሁሉ እውነተኞች ናቸው እውነት ማለት ነው።

ሃያሉ አሏህ ነብዩ ሙሐመድ የነብያቶች ሁሉ መጨረሻ እና መደምደሚያ አድርጎ ለሰውዘር በሙሉ ልኳቸዋል።

መልመጃ ፱

ባዶ ቦታዎችን በተስማሚ ቃላቶች አሟሉ

(ፍጥረቶቹ/የሚማን መሰረቶች / አኗህ)

በመልእክተኞች ማመን_____አንዱ ነው፡፡ ምክኒያቱም _____እና በፍጥረቱ መካከል ያሉ መልእክቱን የሚያደርሱ እና_____ላይ ማስረጃ የሚሆኑ ኛቸው፡፡

በመጨረሻው ቀን ማመን



አመስተኛው መርህ

በመጨረሻው ቀን ማመን ከኢማን መሰረቶች ማመን አንዱ ነው። ይህ ማለት ከሞት በኋላ በሚሆነው ነገር ሁሉ ማመን ነው። ለምሳሌ

- የቀብር ቅጣት እና የቀብር በረከት
- መቀስቀስ ፣ ሚዛንመኖሩን፣ ሽልማት እና ቅጣት መኖሩን
- ጀነት እና ጀሃነም እና ሌሎች አሏህ ስለፍርዱ ቀን የገለፃቸውን ነገሮች በሙሉ

መልመጃ 10

ቀለም መቀባት

በመጨረሻው ቀን ማመን ማለት

ከሞት በኋላ በሚሆነው ነገር ሁሉ ማመን ነው።
የቀብር ቅታት እና የቀብር በረከት
መቀስቀስ ፤ ሚዛን መኖሩን ፤
ሽልማት እና ቅጣት መኖሩን
ጀነት እና ጀሃነም እና ሌሎች አሏህ
ስለ ፍርዱ ቀን በገለፃቸውን ነገሮች
በሙሉ ማመን ነው።

በመለኮታዊ ውሳኔ ማመን



ስድስተኛው መርህ

መለኮታዊ ውሳኔ ወይም ቅድመ ድንጋጌ ማመን ከትላልቅ የኢማን ምሰሶዎች ውስጥ አንዱ ነው።።

ይህ መርህ አራት ደረጃዎች አለት

1ኛ በአሏህ ዘላለማዊ እውቀት ማመን

2ኛ ለህዋል መህፉዝ መዝገብ ላይ ሁሉም ነገር ተፅፏል ብሎ ማመን

3ኛ ሁሉን አቀፍ በሆነው የአሏህ ፈቃድ ማመን

4ኛ በአሏህ ፍጥረታት ማመን

መልመጃ 11

የመለኮታዊ ውሳኔ ወይም ቅድመ ድንጋጌ ደረጃዎችን በተመለከተ የቀረቡ አረፍተ ነገሮችን በቅደምተከተላቸው እነዚህን ቁጥሮች 1 ፣ 2 ፣ 3 ፣ 4 በመጠቀም አስተካክላችሁ ፃፍ

( ) በአሏህ ፍጥረታት ማመን

( ) ሁሉም ነገር ለሀዋል መህፉዝ ላይ ተፅፏል ብሎ ማመን

( ) ሁሉን አቀፍ በሆነው የአሏህ ፈቃድ ማመን

( ) ሁሉም ነገር ከመፈጠሩ በፊት በነበረው ዘላለማዊ በሆነው የአሏህ አውቀት ማመን

ትክክለኛ እምነት፡
የአሏህ መልእክተኛ ሶሃባዎችን በተመለከተ

- የአሏህ መልእክተኛ ሶሃባዎችን መውደድ
- እነሱን መርዳት እና በእነሱ መደሰት
- ለእነሱ ምህረትን መጠየቅ እና እነሱን ማወደስ

ሃያሉ አሏህ እንዲህ አለ፡

“ከስደተኞቹ እና ከረዳቶቹም ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎች እነዚያ በበጎ ስራ የተከተሏቸው አሏህ ከእነሱ ወዷል እነሱም ወደዋል፡፡ በስሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ በውስጣቸውም ዘላለም ይኖራሉ፡፡ ይህ ታላቅ እድል ነው፡፡”

መልመጃ 12

ባዶ ቦታዎችን በተስማሚ ቃላት አሟሉ

(ለእነሱ ምህረት መለመን ፣ በእነሱ መደሰት/ ሶሃባዎችን መውደድ)

ትክክለኛው እምነት ፡ ሃቦችን በተመለከተ

የአሏህ መልእክተኛ_____

እነሱን መርዳት እና_____

_____እና እነሱን ማወደስ


رَبَّنَا تَقَبَّلْ مِنَّا إِنَّكَ
أَنْتَ السَّمِيعُ العَلِيمُ

ማንኛውም አይነት ሃሳብ አስተያየት ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወለልኝ ይችላለ። የወጣቱ ተልዕኮ አህላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.com ይጎብኙና መልዕክት ያስቀምጡልን። ጀዛኩሙሉህ ኸይረን ከሲረን!